Fairfax County PUBLIC SCHOOLS
ENGAGE • INSPIRE • THRIVE

# FCPS ለቨርጂኒያ የአስም የድርጊት መርሃግብር ፈቃድ

**እባክዎ በጀርባ በኩል ያለውን መረጃ እና የአሰራር ቅደም ተከተል ያንብቡ**

## ክፍል I　　በወላጅ ወይም አሳዳጊ የሚሞላ

የፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (FCPS)፣ የፌርፋክስ ካውንቲ ጤና መምሪያ (FCHD) እና የትምህርት እድሜ ህጻናት እንክብካቤ (SACC) ሰራተኞች ይህ ፈቃድ በሚያዘው መሰረት መድሃኒት እንዲሰጡ ፈቃድ እሰጣለሁ። የFCPS፣ FCHD እና SACC አባል ሰራተኞች፣ ከዚህ በታች ባለው የጤና እንክብካቤ አቅራቢው፣ የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ትዕዛዝን የሚያከብሩ ከሆነ፤ ይህን/ይህችን ተማሪ መድሃኒት እንዲጠቀሙ በመርዳት FCPSን፣ FCHDን፣ SACCን፣ እና ማንኛቸውም ሃላፊዎቻቸውን፣ ሰራተኞቻቸውን፣ ወይም ወኪሎቻቸውን ከክስ፣ የይገባኛል ጥያቄዎች፣ ወጪዎች፣ ጥያቄዎች ወይም ድርጊቶች ወዘተ. ነፃ ለማድረግ፣ ለመካስ እና ጉዳት ለማድረስ እንዳልሰሩ ለመውሰድ ተስማምቻለሁ። ። **በዚህ ቅጽ ጀርባ ላይ የተዘረዘሩትን ሂደቶች አንብቤ እንደ አስፈላጊነቱ ኃላፊነቱን እወስዳለሁ። የተሞላ የቨርጂኒያ አስም የድርጊት መርሃ ግብር አቅርቤያለሁ።**

ተማሪው/ዋ ከዚህ በፊት ይህንን መድሃኒት ወስደው ያውቃሉ?　☐ አዎ　☐ የለም　(የለም ከሆነ፣ ተማሪው/ዋ አሉታዊ ምላሽ እንደሌላቸው ለማረጋገጥ የመጀመሪያው ሙሉ መጠን (ዶዝ) በቤት ውስጥ መሰጠት አለበት።)

የመጀመሪያ ዶዝ ተሰጥቷል፡　የተሰጠበት ቀን ______________　ሰዓት ______________

| የተማሪ ስም: የአያት | የመጀመሪያ | የአባት |
|---|---|---|
| | | |

| የልደት ቀን | የትምህር ቤት ስም | የትምህርት አመት | የትምህርት ደረጃ:- |
|---|---|---|---|
| | | | |

ርዕሰመምህሩ/ሯ ወይም የእሱ ወይም የእሷ ተወካይ ሁሉንም አስፈላጊ ማጽደቂያዎች በግል ካልገመገሙ በስተቀር፤ ማንኛውም የትምህርት ቤት ቦርድ ሰራተኛ፣ የህዝብ ጤና ነርስ ወይም የትምህርት ቤት ጤና ረዳት፣ በትምህርት ቦርድ ፖሊሲ የተለየ ሁኔታ መሰረት መድሃኒት ወይም ህክምና መስጠት የለባቸውም። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በትዕዛዙ ላይ የቀረበውን መረጃ ለማብራራት ከዚህ በታች በስም የተጠቀሱትን የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎችን ለማነጋገር ፈቃድ ሰጥቻለሁ።

______________________　______________________　______________________
የወላጅ ወይም አሳዳጊ ፊርማ　　የቀን ስልክ　　ቀን

## ክፍል II　　መመሪያ

**አረንጓዴ ዞን**

- በትምህርት ቤት ምንም አይነት ተግባራት አያስፈልጉም

**ቢጫ ዞን**

- በ **ቢጫ ዞን** የታዘዘ የሚረጭ(ጩ) በአፍ የሚወሰድ መድሃኒት (ኢንሄለር) ወይም የኒቡላይዘር **ነፍስ አድን መድሃኒት** ሕክምናን ይስጡ
- ምልክቶቹ በማንኛውም ጊዜ ከተባባሱ ወይም በ15 ደቂቃ ውስጥ ካልተሻሻሉ ወደ **ቀይ ዞን** ይሂዱ
- ምልክቶቹ ከተሻሻሉ ነገር ግን በ20 ደቂቃ ውስጥ ወደ **አረንጓዴ ዞን** ካልተመለሱ፤ ተማሪውን/ዋን እንዲወስዷቸው ወላጅ/አሳዳጊን ያግኙ፤ ምልክቶቹ
- ከተሻሻሉ እና በ20 ደቂቃ ውስጥ ወደ **አረንጓዴ ዞን** ከተመለሱ፣ ተማሪውን/ዋን ወደ ክፍል ይመልሷቸው
- በ **ቢጫ ዞን** ተማሪው/ዋ ከምልክቶች ጋር ከተመለሱ፣ ነገር ግን ለሁለተኛ ዶዝ ጊዜው ገና ከሆነ፤ ተማሪውን/ዋን እንዲወስዱ ወላጅ/አሳዳጊን ያግኙ

**ቀይ ዞን**

- በ **ቀይ ዞን** የታዘዘ የሚረጭ(ጩ) በአፍ የሚወሰድ ወይም የኒቡላይዘር **ነፍስ አድን መድሃኒት** ሕክምናን ይስጡ
- EMS/911 ይደውሉ
- ቤተሰብ/አሳዳጊን ያግኙ
- EMSን እየጠበቁ እያለ፣ የነፍስ አድን መድሃኒትን በየ15 ደቂቃው ለሶስት ህክምናዎች ይስጡ
    - **በቢጫ ዞን** የተሰጠው ህክምና የእነዚህ ሶስት ህክምናዎች አካል ተደርጎ **<u>አይቆጠርም</u>**

**ማሳሰቢያ፡ ተማሪው/ዋ በሃኪማቸው የተሞላ ወቅታዊ የቨርጂኒያ የአስም የድርጊት መርሃ ግብር ያላቸው ከሆነ እና ነገር ግን የታዘዘላቸው <u>አልቡተሮል</u> ከሌላቸው፤ የትምህርት ቤቱን መለያ ያልተፃፈበት የአልቡተሮል እና ቫልቭድ ሆልዲንግ ቻምበር አቅርቦት ክምችት በመጠቀም፣ የተማሪውን/ዋን እቅድ ይከተሉ።**

| | |
|---|---|
| ☐ **<u>ይህን ክፍል በአፍ የሚወሰድ መድሃኒት እራሳቸው ለሚይዙ እራሳቸው ለሚወስዱ ተማሪዎች ይሙሉ</u>**<br>ተማሪው/ዋ ፈቃድ ባለው ሃኪም በአፍ የሚወሰድ መድሃኒት በትምህርት ቤት የመያዝ እና በራሳቸው የመጠቀም ስልጣን ተሰጥቷቸዋል። በርዕሰ መምህሩ/ሯ እውቅና፣ ተማሪው/ዋ በትምህርት ወይም SACC ሰዓታት በአፍ የሚወሰድ  መድሃኒት ይይዛሉ። ተማሪው/ዋ በአፍ የሚወሰድ መድሃኒት የመያዝ ሃላፊነት እንደሚወስዱ ይረዳሉ፤ እንዲሁም በቨርጂኒያ የአስም የድርጊት መርሃ ግብር ላይ እንደተገለፀው፤ ፈቃድ ባላቸው ሃኪም የተሰጠውን ትዕዛዝ ለማክበር ይስማማሉ። ( እንደ ተጠባባቂ የሚወሰድ ተጨማሪ በአፍ የሚወሰድ መድሃኒት በትምህርት ቤት የጤና ክፍል ወይም በሌላ እውቅና የተሰጠው የትምህርት ቤት ቦታ ሊቀመጥ ይችላል።) | ______________________　____________<br>የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ (ያስፈልጋል)　ቀን<br><br>______________________　____________<br>የተማሪ ፊርማ (ያስፈልጋል)　ቀን |

## ክፍል III　　በርዕሰ መምህር ወይም በርዕሰ መምህር ተወካይ የሚሞላ

እንደአስፈላጊነቱ √ ምልክት ያድርጉ:

☐ ከላይ ያለው የቨርጂኒያ የአስም የድርጊት መርሃ ግብር ክፍል I ፊርማን ጨምሮ ተሞልቷል።

☐ መድሃኒቱ በተገቢው ሁኔታ ምልክት ተደርጎበታል። ______________________ጥቅም ላይ ያልዋለ ማንኛውም መድሃኒት በወላጅ ወይም አሳዳጊ የሚወሰድበት ቀን።
(የዚህ ፈቃድ አገልግሎት ከተጠናቀቀበት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ወይም በትምህርት የመጨረሻው ቀን።)

______________________　______________________
ርዕሰ መምህር ወይም የርዕሰ መምህር ተወካይ　　ፊርማ　　ቀን

ከፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪ ስኮላስቲክ መዝገብ የሚላክ መረጃ፤ ከወላጅ ወይም ብቁ የሆነ/ች ተማሪ የጽሁፍ ፍቃድ ከሌለ በስተቀር፣ ተቀባዩ ይህን መረጃ ማንኛውም ሌላ አካል እንዲያገኘው ላለመፍቀድ በተስማሙበት ሁኔታ ነው።

## የአስም ነፍስ አድን መድሃኒት ቅደም ተከተልን የተመለከተ መረጃ ለወላጅ/አሳዳጊ

1. የአስም ነፍስ አድን መድሃኒት በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ በሚሰጣቸው እንቅስቃሴዎች፣ ወይም በSACC ሊሰጡ የሚችሉት ፈቃድ ያላቸው ሃኪም እና ወላጅ ወይም አሳዳጊ ሁለቱም በፈረሙበት ፈቃድ ብቻ ነው።

2. በቨርጂኒያ የአስም የድርጊት መርሃ ግብር ፈቃድ ያላቸው የሃኪም ትዕዛዝን ማግኘት የወላጁ/ጇ ወይም አሳዳጊው/ዋ ሃላፊነት ነው። ቅፁ እዚህ ሊገኝ ይችላል፡ ቨርጂኒያ የአስም የድርጊት መርሃ ግብር

3. ወላጁ/ጇ ወይም አሳዳጊው/ዋ የተማሪቸውን የአስም ነፍስ አድን መድሃኒት እና የተሞላውን የቨርጂኒያ አስም የድርጊት መርሃ ግብር ወደ ትምህርት ቤት ሲያመጡ ይህን የSS/SE-65 ቅጽ ይሞላሉ።

4. ፈቃድ ያለው ሃኪም የቨርጂኒያ አስም የድርጊት መርሃ ግብርን በመሙላት ፋንታ የቢሮ የጽህፈት መሳሪያዎችን ወይም የሐኪም ማዘዣ ወረቀትን መጠቀም አይችሉም።

5. የመድኃኒት ማዘዣ ናሙናዎች በተለምዶ በመድሃኒት መለያ ላይ የሚታተም መረጃን በማካተት ፈቃድ ባለው ሐኪም በትክክል መሰየም አለባቸው።

6. **የማንኛውም አዲስ መድሃኒት የመጀመሪያ መጠን (ዶዝ) በቤት ውስጥ መሰጠት አለበት።**

7. ወላጅ ወይም አሳዳጊ በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ፤ እንዲሁም በሚሰጠው የመድኃኒት መጠን ላይ ወይም መድሃኒት በሚወሰድበት ሰዓት ላይ ለውጥ በሚኖርበት ወቅት፣ ለትምህርት ቤቱ ወይም ለSACC አዲስ ቅፅ የማቅረብ ሃላፊነት አለባቸው።

8. ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤት እና በSACC ሰዓታት እንዲወስዱ ካልተፈቀደላቸው በስተቀር፤ የአስም መድህን መድሀኒት በወላጅ ወይም በአሳዳጊ ለትምህርት ቤቱ ጤና ክፍል በእጅ መቅረብ አለበት።

9. ተማሪው/ዋ በትምህርት ሰዓት እንዲይዙት ካልተፈቀደላቸው በስተቀር፤ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚቀመጠው መድሃኒት ለተፈቀደላቸው ሰዎች ብቻ ተደራሽ በሆነ በተቆለፈ ቦታ ይከማቻል። አንድ ተማሪ የራሱን/ሷን በአፍ የሚወሰድ መድሃኒት ከያዙ፣ መጠባበቂያው በትምህርት ቤቱ የጤና ክፍል ውስጥ ሊቀመጥ ይችላል።

10. የዚህ ፈቃድ አገልግሎት ከተጠናቀቀበት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ወይም በትምህርት የመጨረሻው ቀን፤ ተማሪው/ዋ እንዲይዙ ካልተፈቀደላቸው በስተቀር፣ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ማንኛውንም ጥቅም ላይ ያልዋለን የመድኃኒት ክፍል መውሰድ አለባቸው። በዚያ ጊዜ ውስጥ የእኔ ነው የሚል የሌላቸው መድሃኒቶች እንዲጠፉ ይደረጋሉ።

11. የፌርፋክስ ካውንቲ የጤና ዲፓርትመንት፣ የፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የፌርፋክስ ካውንቲ የትምህርት ዕድሜ የህፃናት እንክብካቤ፤ ተማሪው/ዋ በራሳቸው ለሚወሰዱት የተፈቀደ መድሃኒት ሃላፊነት አይወስዱም።

12. በምንም አይነት ሁኔታ ማንኛውም የጤና ሰራተኛ ወይም የትምህርት ቤት ወይም የSACC ሰራተኛ ማንኛውንም መድሃኒት እዚህ ከተዘረዘሩት የአሰራር ሂደቶች ማዕቀፍ ውጭ እና/ወይም ከFCPS ደንብ ውጭ ሊሰጥ አይችልም።

13. ወላጁ/ጇ ወይም አሳዳጊው/ዋ በትምህርት ቀን እና በSACC መሰጠት ለሚያስፈልገው መድሃኒት ለFCPS እና SACC የመድሃኒት አቅርቦት ማቅረብ አለባቸው።